መልእክት ሦስት

**በሳሙኤል ታሪክ ውስጥ የታዩ**
**መንፈሳዊ መርሆች፣ የሕይወት ትምህርቶች እና ቅዱስ ማስጠንቀቂያዎች**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ 1 ሳሙ. 1፡10-11፣ 18-20፣ 27-28፤
2፡30፣ 35-36፤ 3፡1-21፤ 4፡11-22፤ 7፡3-17፤ 12፡23

**I. ሳሙኤል ከሌዊ ነገድ ነበረ (1 ዜና. 6፡33-38) ነገር ግን በእግዚአብሔር የተወሰነው የካህናት ቤተሰብ ከሆነው ከአሮን ቤተሰብ አልነበረም፤ ሳሙኤል በውልደት ሳይሆን በናዝራዊ ስእለት በሆነ ክህነት እግዚአብሔርን አገለገለ፦**

ሀ. የሐናን ጸሎት ከመመለስ ጋር የነበረው የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ የእግዚአብሔርን መሻት ለመፈጸም ፍጹም የሆነን ድል ነሺ ናዝራዊ ለማፍራት ነበረ፤ ከመወለዱ በፊት እንኳ ሳይቀር ሳሙኤል እንደዚህ አይነት ሰው ለመሆን በእናቱ ተሰጥቶ ነበረ—1 ሳሙ. 1፡10-11፣ 18-20።

ለ. እግዚአብሔር ሕዝቡ በሙሉ ናዝራዊያን እንዲሆኑ ይፈልጋል፤ ናዝራዊ መሆን ማለት ለእግዚአብሔር ፍፁም በሆነ መንገድና እስከመጨረሻው ድረስ መቀደስ፣ መለየት ነው፣ ማለትም፣ ከእግዚአብሔር ውጪ ለሌላ ለምንም ነገር እንዲሁም ከእርካታው—እንደ ክርስቶስ ምስክርና መገለጥ የምትመሰክር ቤተ ክርስቲያን ከሆነችው ከኢየሱስ ምስክር—ውጪ ለሌላ ለምንም አለመሆን ነው—ዘኁ. 6፡1-2፤ መዝ. 73፡25-26፤ ራእ. 1፡2፣ 9-13፤ 19፡10፤ ተዛ. ዘጸ. 38፡21፦

1. ናዝራዊ ከወይን ጠጅ እና ምንጩ የወይን ጠጅ ከሆነ ከማናቸውም ነገር መታቀቡ የሚያመለክተው ከሁሉም አይነት ምድራዊ ድሰታዎችና ፍስሃዎች መታቀብ እና ክርስቶስን እንደ ድሰታውና ፍስሃው መውሰድንና መደሰትን ነው፤ የሕይወት ዛፍን መብላት፣ ማለትም፣ ክርስቶስን እንደ ሕይወት አቅርቦታችን መደሰት በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ቀዳሚው ጉዳይ መሆን አለበት—ዘኁ. 6፡3-4፤ ራእ. 2፡7፤ መሳ. 9፡12-13።
2. ናዝራዊ ጸጉሩን አለመላጨቱ የሚያመለክተው የጌታን ራስነት እንዲሁም በእግዚአብሔር የተሾሙትን ወኪል ሥልጣናትን ሁሉ አለመቀበልን ሳይሆን ሙሉ በሙሉ መገዛትን ነው—ዘኁ. 6፡5፤ ሮሜ. 13፡1-2፤ ኤፌ. 5፡21፣ 23፤ 6፡1፤ ዕብ. 13፡17፤ 1 ጴጥ. 5፡5።
3. ናዝራዊ በሥጋ ዘመዶቹ ሞት አለመርከሱ ይልቁንም ለእግዚአብሔር ቅዱስ ለመሆን በመለየት መቆየቱ የሚያሳየው ናዝራዊው ተፈጥሮአዊ ፍቅርን ድል መንሳቱን ነው—ዘኁ. 6፡7።
4. ናዝራዊ ወደ ሞተ ሰው አለመቅረቡና አጠገቡ ድንገት በሞተ ነገር አለመርከሱ የሚያሳየው ናዝራዊው ከሞት የተለየ መሆኑን ነው—ቁ. 6-9፣ ራእ. 3፡4፤ ዘሌ. 11፡31፤ 5፡2፤ ተዛ. 1 ዮሐ. 5፡16።

**II. በሳሙኤል ጊዜ፣ የአሮን ቤት ክህንነት ፈጽሞ ወድቆ ነበረ፤ ሆኖም ግን፣ እግዚአብሔር ሁኔታውን አስቀድሞ አይቶ ነበረ፤ የአሮን ቤት ካህናት እንዲሆኑ ከመወሰኑ ጎን ለጎን ፣ በሚሾሙት ካህናት ዘንድ አለመብቃት በሚያጋጥምበት ጊዜ ተጨማሪ ነገርን—በዘኁልቁ 6 ያለውን የናዝራዊ ስእለትን—አደረገ፦**

ሀ. የአሮን ቤት ሲወድቅ፣ ይህ ተጨማሪ ነገር ተግባራዊ ጥቅም ላይ ዋለ፣ ሳሙኤል በመሰጠት፣ በመለየት እና ለእግዚአብሔር እንዲሆን በመሰጠት ካህን ሆነ—1 ሳሙ. 1፡11፣ 27-28።

ለ. በዔሊ ጊዜ ክህንነቱን በተመለከተ እግዚአብሔር ድሃ ነበረ፤ ስለዚህም ሐና ሳሙኤልን ለጌታ እንዲሆን ሰጠችው፤ ሁኔታው ጤናማ በማይሆንበት ጊዜ፣ ጌታ አስተዳደሩን በተመለከተ ድሃ ይሆናል፣ እናም አንድ ሰው ራሱን በፈቃደኝነት ለጌታ እንዲሆን መስጠቱ አስፈላጊ ይሆናል።

ሐ. ሳሙኤልን ለዔሊ ካቀረበችው በኋላ፣ ሐና ድንቅ በሆኑ ሥራዎቹ ስለተከናወኑት ማዳኖቹ እግዚአብሔርን አመሰገነች፤ ጸሎቷ እግዚአብሔር በኢኮኖሚው ካለው እንቅስቃሴ ጋር የተገናኘ እና የእግዚአብሔርን ኢኮኖሚ በተመለከተ የሆነ ነገርን እንደተገነዘበች የሚጠቁም ነበረ—2፡1-10።

**III. ሳሙኤል በዔሊ ጥበቃ ሥር አደገ፤ እግዚአብሔርን የማገልገልን መንገድ በዔሊ በመማር (ቁ. 11፣ 18-19)፣ ሳሙኤል በልጅነቱ በዔሊ ፊት እግዚአብሔርን አገለገለ፦**

ሀ. እግዚአብሔር ሳሙኤልን ሦስት ጊዜ ጠራው፤ “ዔሊም እግዚአብሔር ብላቴናውን እንደ ጠራው አስተዋለ። ዔሊም ሳሙኤልን። ሄደህ ተኛ ቢጠራህም፦ አቤቱ፥ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር በለው አለው። ሳሙኤልም ሄዶ በስፍራው ተኛ። እግዚአብሔርም መጥቶ ቆመ፥ እንደ ቀድሞውም፦ ሳሙኤል ሳሙኤል ብሎ ጠራው። ሳሙኤልም፦ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር አለው”—3፡1-10፦

1. ይህ ሳሙኤል ከዔሊ የተማረው ሙሉበሙሉ አዎንታዊ የሆነ ነገር ነው፤ እንደ ጌታ አገልጋዮች፣ ሁልጊዜ እርሱን በመስማት ከእርሱ ጋር ያለንን ኅብረት መጠበቅ አለብን—ሉቃ. 1፡34-38፤ 10፡38-42።
2. ሕይወታችን የሚመረኮዘው በጌታ ቃሎች ላይ ነው፤ ሥራችን ደግሞ የሚመረኮዘው በትእዛዛቱ ላይ ነው (ራእ. 2፡7፤ 1 ሳሙ. 3፡9-10፤ ተዛ. ኢሳ. 50፡4-5፤ ዘጸ. 21፡6))፤ የአማኞች ሕይወት ሙሉበሙሉ ከጌታ ንግግር ጋር የተያያዘ ነው (ኤፌ. 5፡26-27)።
3. የጌታ ንግግር እንደ እርሱ አምሳያ ሙሽራይቱን ማግኘት የሆነውን የዘላለማዊ ኢኮኖሚውን ግብ እንድንፈጽም ያስችለናል—ራእ. 2፡7፤ ኤፌ. 5፡26-27፤ መኃ. 8፡13-14።

ለ. ሳሙኤል ሲማር ሳለ፣ አሮናዊው ክህነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበላሸ እንደሆነ ተመለከተ፡-

1. የእግዚአብሔር ታቦት በሕዝቡ ሽማግሌዎች ያለ አግባብ ጥቅም ላይ ሲውል እና በፍልስጤማውያን ሲማረክ አየ የእግዚአብሔርም ክብር ሲሸሽ አየ፤ የዔሊን እና የሁለቱ ልጆቹን፣ የአፍኒንና የፊንሐስ መሞትን ያካተተውን በዔሊ ቤት ላይ የሆነውን የእግዚአብሔርን የከፋ ፍርድ ተገነዘበ—1 ሳሙ. 2፡12-36፤ 4፡11-22።
2. በዔሊ ቤት የሆነው የእግዚአብሔርን የከፋ ፍርድ በእግዚአብሔር ሰው ተተንብዮ ነበረ (2፡27-36)፤ ከዚያም፣ ይህ የከፋ ፍርድ በሳሙኤል በኩል በተነገረው የያህዌ ቃል ተረጋገጠ (3፡11-18)።
3. ስለሚመጣው ፍርድ እግዚአብሔር በሳሙኤል በኩል ለዔሊ የመናገሩ አላማ በዚህ ወጣት ካህናዊው ልጅ ላይ የማይረሳ ስሜትን ለመፍጠር ሊሆን ይችላል፤ ይህ የእግዚአብሔር ጥበብ ነበረ—ቁ. 17-18።
4. ይህ ሳሙኤልን በፊቱ ከነበረው ከናዝራዊ ክህንነቱ አላደከመውም፣ ይልቁንም በሕይወቱ በሙሉ ለእግዚአብሔር ባለው አገልግሎቱ ንጹህ ሆኖ እንዲቆይ የረዳው ቀጣይነት ያለው ማስጠንቀቂያ ሆነ።

## IV. ሳሙኤል ዘመኑን ከንግሥና ጋር ወደ መንግሥቱ ዘመን የቀየረ ሰው ነበረ፤ ይህ በእስራኤል ታሪክ ብቻ ሳይሆን በሰው ዘር ታሪክም ጭምር ታላቅ ነገር ነበረ፡-

ሀ. ሳሙኤል በአሮን ቤት ላይ አላመጸም፣ ከአሮን ቤት የሆነ ምንም ነገር ያለአግባብ አልወሰደም፤ ሳሙኤል እያደገ ሲሄድ እግዚአብሔር ዘመኑን ከመንግሥቱ ጋር ወደ ንጉሥ ዘመን ለመቀየር ያስችለው ዘንድ የሚያስፈልገውን ነገር በሙሉ ለማድረግ እርሱን ፍጹም ያደርግና አቅሙን ይገነባ ዘንድ ከባቢ ሁኔታን አዘጋጀ።

ለ. እንደ ካህን ሳሙኤል ያረጀውን እና የሻገተውን የአሮንን ክህንነት ተካ፣ አቆመውም፤ እግዚአብሔር መንግሥቱን ለማምጣት በአመጽ ወይም በአብዮት ሳይሆን በመለኮታዊ መገለጥ ዘመኑን ለመቀየር ሳሙኤልን ተጠቀመ።

ሐ. ሳሙኤል የመገለጥ ሰው ነበረ፣ ሁሉንም ነገር ያደረገው ባየው ነገር መሠረት ነበረ፤ "እግዚአብሔርም ደግሞ በሴሎ ተገለጠ፤ እግዚአብሔርም በእግዚአብሔር ቃል ለሳሙኤል በሴሎ ይገለጥ ነበር" (ቁ. 21)፤ በተጨማሪም ሳሙኤል በእግዚአብሔር ልብ መሠረት—የእግዚአብሔር ልብ ቅጂ፣ ብዜት የሆነ ሰው ነበረ፤ እንዲህ አይነት ሰው በመሆኑ፣ አመጽ የሆነ ምንም ነገር ከቶ አያደርግም።

## V. የሳሙኤል ድርጊቱ፣ ኑሮው እና ሥራው ብቻ ሳይሆን እርሱ የሆነው ነገር በሙሉ እና ማንነቱ በእግዚአብሔር መሠረት ነበረ፤ የሳሙኤል ማንነትና የእግዚአብሔር ልብ አንድ ነበሩ፤ በዚህም ምክንያት፣ በእግዚአብሔር መሠረት የሆነው ሳሙኤል፣ በምድር ላይ የነበረ የእግዚአብሔር ወኪል ነበረ ማለት እንችላለን፡-

ሀ. ሳሙኤል ትኩረት የሚሰጠው ለእግዚአብሔር ኃሳብ ነበረ፤ ሌላ ሃሳብ፣ የሚያሰላስለው ነገር ወይም አስተሳሰብ አልነበረውም፤ ኑሮውና ሥራው በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ላለው ነገር መከናወን ነበረ።

ለ. ሳሙኤል ነገሥታት ይሆኑ ዘንድ ሳኦልንና ዳዊትን ቀባ (10፡1፤ 16፡1፣ 13)፤ ይህ በእግዚአብሔር በተወሰነው መሠረት ሳሙኤል ንጉሡ ምን ያደርግ እንደነበረ በመመልከት ንጉሡን ለመከታተል እና ለመምራት ያለማቋረጥ በእግዚአብሔር በተቀባው ፊት ይሄድ ዘንድ ነበረ (2፡35)።

ሐ. ይህ የሚያመለክተው ሳሙኤል፣ በምድር ላይ የነበረው የእግዚአብሔር ወኪል ከንጉሡ ይበልጥ እንደነበረ ነው፤ ሳሙኤል ይህን ያህል ብቁ መሆን የቻለው እግዚአብሔር ልዩና ብቸኛ በሆነ መንገድ ለኢኮኖሚው ለብዙ ዓመታት ፍፁም ሲያደርገው ስለነበረ ነው፡-

1. ሳሙኤል ለራሱ የሚሻ ወይም ለራሱ ጥቅም የሚያስበው ነገር የሌለው በእግዚአብሔር መሠረት እና እንደ እግዚአብሔር ልብ የሆነ ሰው ስለነበረ እግዚአብሔር ኢኮኖሚውን ለማከናወን ሊጠቀመው ችሏል—ተዛ. ማቴ. 16፡24-26፤ ሉቃ. 9፡23-25።
2. ከእግዚአብሔር ልብና ከእግዚአብሔር ምርጦች ውጭ ለሆነ ማንኛውም ነገር ልብ አልነበረውም፤ ልቡ የእግዚአብሔር ልብ መንጸባረቅ ነበረ—ተዛ. ፊልጵ. 2፡19-22፤ 2 ቆሮ. 3፡16-18።

3. ሳሙኤል የእግዚአብሔር የግል ሃብቱና ንብረቱ ስለሆኑት ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ አለመጸለይን በያህዌ ላይ እንደሚደረግ ኃጢአት አድርጎ ቆጠረ—1 ሳሙ. 12፡23፤ ዘጸ. 19፡5።

መ. ምንም እንኳ እርሱ በነበረበት ከባቢ ሁኔታ ለእግዚአብሔር መቆም ለሳሙኤል ቀላል ባይሆንም፣ ለእግዚአብሔር ፍላጎት ግድ ተሰኘ፣ ዘመኑንም ቀየረ፤ በብሉይ ኪዳን መሠረት ለእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ልብ ከመሆን አንጻር ከሙሴ ጋር በእኩል ደረጃ ተቀምጧል—ኤር. 15፡1።

ሠ. "ሳሙኤልም የመንግሥቱን ወግ ነገረ፥ በመጽሐፍም ጻፈው በእግዚአብሔርም ፊት አኖረው"—1 ሳሙ. 10፡25፦

1. ሙሴ ለእስራኤል ልጆች ሕጉን ሰጠ፣ ሆኖም ግን ሳሙኤል ከመምጣቱ በፊት የሚመሩበት መተዳደሪያ ደንብ፣ ሕገ መንግሥት አልነበራቸውም።
2. ሳሙኤል የእግዚአብሔርን መንግሥት በምድር ላይ እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉ መተዳደሪያ ደንቡን፣ ሕገ መንግሥቱን፣ ተግባሩን፣ ልማዶቹን፣ ሥርዓቶቹን፣ ትእዛዛቱን፣ እና ሕጎቹን ለሕዝቡ አስተማረ።

## VI. እግዚአብሔር የዘቀጠውን ክህንነት ለመተካት ወጣቱን ናዝራዊ ሳሙኤልን እንደ ታማኝ ካህን በማስነሣት አዲስን ዘመን ጀመረ—2፡35፦

ሀ. ሳሙኤል በአሮጌው ክህንነት የነበረውን የእግዚአብሔርን ቃል ትምህርት ለመተካት የእግዚአብሔርን ቃል ይናገር ዘንድ በእግዚአብሔር ተሾመ፤ በክህንነት ካህኑ ማድረግ ያለበት የመጀመሪያው ነገር ለእግዚአብሔር መናገር ነው።

ለ. በሊቀ-ካህኑ የሚለበሱት የፍርዱ ደረት ኪስ እንዲሁም ኡሪም እና ቱሚም እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚናገርባቸው መንገዶች ነበሩ (ዘጸ. 28፡30)፤ በክህንነቱ መዝቀጥ የእግዚአብሔር ንግግር ሊጠፋ ተቃርቦ ነበር (1 ሳሙ. 3፡1፣ 3)።

ሐ. እግዚአብሔር ከፍ በተደረገው ክህንነት ሳሙኤልን እንደ ነብይ በማጽናት ለመረጠው ሕዝብ ቃሉን አገለገለ (ቁ. 20-21)፣ ሳሙኤልን እንደ ፈራጅ በማስነሣት በተመረጠው ሕዝቡ ላይ ሥልጣኑን አንቀሳቀሰ (7፡15-17)።

መ. እንደ የመጨረሻው ፈራጅ፣ ሳሙኤል ፈራጅነትን አቆመ፣ እንደ አዲሱ ካህን ከፍ በተደረገው ክህነት የጠነከረውን ንግሥና አመጣ።

ሠ. እግዚአብሔር ለእርሱ ይናገር ዘንድ ሕያው የሆነ ሰው፣ ካህን ማስነሣት አስፈልጎት ነበረ፤ እግዚአብሔር በወሰነው መንገድ ለእግዚአብሔር ንግግር ክህንነትን ስላመጣ ሳሙኤል የመጀመሪያው ነብይ ተደርጎ ይቆጠራል—ሐዋ. 3፡24፤ 13፡20፤ ዕብ. 11፡32።

## VII. ሳሙኤል በምድር ላይ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ነበረ፤ በምድር ላይ እንደነበረ የእግዚአብሔር ወኪል፣ በምድር ላይ ሕዝቡን ለማስተዳደር በሰማይ እንዳለው የእግዚአብሔር ተወካይ፣ ሳሙኤል በአምስት ስፍራዎች አገለገለ —1 ሳሙ. 7፡3፦

ሀ. ሳሙኤል እንደ ናዝራዊ፣ ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መፈጸም ሙሉበሙሉ እንደተሰጠ ሰው አገለገለ—1፡11፣ 28።

ለ. ሳሙኤል የሻገተውን እና የዘቀጠውን ክህንነት ለመተካት እግዚአብሔርን እንሚያከብርና፣ እግዚአብሔርን እንደሚያስደስት ካህን አገለገለ፣ በምድር ላይ ላለው መለኮታዊ አገዛዝ ንጉሥን እስከመሾምና እስከማጽናት ድረስ አንኳ ሳይቀር በእግዚአብሔር ፈንታ ለመሥራት ታማኝ ነበረ—2፡30፤ 35-36፤ 7፡3-17፤ መሳ. 9፡9፤ 13።

ሐ. ሳሙኤል፣ የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ በነበረበትና ራእዮች ባልተለመዱበት ጊዜ (1 ሳሙ. 3፡1-10፤ 19-21) የአሮጌውን ክህንነት ትምህርት ለመተካት የእግዚአብሔርን ቃል ለመናገር በእግዚአብሔር እንደ ተሾመ ካህን አገለገለ (3፡20)።

መ. ሳሙኤል በአሮጌውና በሻገተው ክህንነት የነበረውን የሕዝቡን መፈረድ ለመተካት በንግሥናው እውነታ እንደ ፈራጅ አገለገለ—7፡15-17።

ሠ. ሳሙኤል እግዚአብሔር ለምርጦቹ ባለው ፈቃዱ ውስጥ ያለው መሻቱ ይፈጸም ዘንድ በእግዚአብሔር መንገድ እንዲጠበቁ፣ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ እንዲሆኑ፣ በአሕዛብ ጣዖታት ወጥመድ ውስጥ እንዳይወድቁና እግዚአብሔርን እንደ አቤንኤዘር (ትርጓሜው "የእርዳታ ዓለት"—ቁ. 12) እንዲያደስቱት ለእግዚአብሔር ምርጦች እንደሚጸልይ እንደ የጸሎት ሰው አገለገለ (ቁ. 3-17፤ 8፡6፤ 12፡19-25፤ 15፡11)።

*© 2021 Living Stream Ministry*